እንባ ይብዛበት እንዴ?!

(ለክቡር ድምጻዊ ጥላሁን ገሠሠ ስንብት)

ለሀገሩ ክብር በእንባ እየታጠበ ፍቅርን ላስተማረ፣
ግብሩ ተከፈለ፤ የሚሊዮኖች እንባ በፍቅር ተቸረ፤
ቃሉን የጠበቀ ላገር ለወገኑ በክብር የጸና፣
እንባ ይብዛበት እንዴ?! የምዕተ-ዓመት ጀግና!

የዝምድናን አዚም የሕይወትን ምስጢር በድምጹ ለውሶ፣
በመለኮት ኃይል ለኢትዮጵያዊ ሁላ ነበር ለካ አጉርሶ?
ጉድ ነው ያልታሰበ በእናት ሀገር ታሪክ ፈጽሞ ያልታየ፤
ተጣብቆት እሚኖር የገዛ አካሉ ሥጋ እንደተለየ. . .፣
ሰውነቱ ርዶ መናገር ተስኖት ሁለት ዐይኑን ጨምቆ፣
በመላ ዓለም ዙሪያ ሐበሻ አለቀሰ ካንጀት ተንሰቅስቆ፡፡

የሬድዮ፣ የቲቪ.. ሪፖርተር ሥራ አጣ ዘገባ አስጨነቀ፣
ጥሌ የጨበጣትን ማይክራፎን ፈርቶ ሁሉ ተሳቀቀ፤
መች ጠፍቶ እሚጠየቅ በስልክ በስቱዲዮ ሰልፉማ ተመመ፣
ስለእርሱ እሚያስረዳ «ባለሙያ ታጣ» እንባ እየቀደመ፤
በሲቃ ታብተው ቃላትም አደሙ፣
ዜና ጋዜጠኞች እንባ አስተረጎሙ!

ባለዝና ሃብቱን ዕንቁ ድምጽ ዕሴቱን...
ሳይሰስት ሳይሳሳ ሲለግስ ኖረና፣
በስተመጨረሻ ወለዱን አስቦ በእንባ አስከፈለ እርግፍ አረገና!
ምድርን ሲያንቀጠቅጥ ገኖባት የኖረ የመድረኳን አምባ፣
ከዕይታ ሲሰወር አሻፈረኝ ብሎ ከሥራ ሲገባ፤
ፍቅር የተራበ ሕይወት የተጠማ.. ቀን የጎደለበት ምነው አያነባ?!

አዛውንት፣ ወጣቱ. . . መላ ሕዝበ-ኢትዮጵያ
ለመከራው መግቻ ለሃዘኑ መጽናኛ..
ለደስታው ጡዘት ለፍቅሩ መዝናኛ፣
ከውልደት እስከ ዕድገት የሕይወት መንፈስ ድምጽ ሲመገብ የኖረው፣
ድምጽ-አልባ ሆነና ታላቁን ድምጻዊ ጥላሁን ገሠሠን በእንባ ስንቅ ሸኘው!

ጌታቸው አበራ
ሚያዚያ ፪ ሺ ፩ ዓ.ም
(ኤፕሪል 2009)